የ፳፻፪ ትክክለኛ ምርጫ ልሣን
ምርጫው በጕዥው ክፍል ተዘጋጅቷል።
ሕዝቡ ያለውዴታው ይሣተፋል።
የእኛም አስተዋፅዖ እነሆ።

# እስከመቼ

ጥር ፴ እስከ የካቲት ፮ ቀን ፳፻፪ ዓ. ም.
February 7 to February 13, 2010
ቅፅ ፩ ቁጥር ፬
Volume I Number 4

## የምርጫ ቦርዱን ነፃነት አስመልክቶ

እዚህ ላይ፤ በመግቢያችን መግቢያ ላይ፤ የሀገሪቱን አጠቃላይ የአስተዳደር ዘይቤ መዳሰሱ፤ በጠቅላላ በህዝቡ ሥነልቡና የሚሽከረከረውን ውስጣዊ የፖለቲካ አመለካከት በግልፅ ይነግረናል። በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ማን ያገኛል? ለትምህርት ወደ ውጭ ማን ይላካል? በመንግሥት ሥር ያሉ ኮርፖሬሽኖችን እነማን ይመራሉ? የመከላከያ ሠራዊቱን የላዕላይ መዋቅር የያዙት እነማን ናቸው? እነኚህን ጥያቄዎች ማቅረባችን፤ ተመሳሳይ መልስ የሚሰጠውን የምርጫ ቦርድ አባላትን መመዘኛ ነጥብ ለማሣየት ይረዳል ብለን ስላመን ነው።

ወደሀገሪቱ ገዢ ፓርቲ የፖለቲካ ፍልስፍናና የአስተዳደር ዘይቤ እንመስ። የገዢው ፓርቲ አመራር በህዝቡ ላይ ዕምነት የለውም። በምርጫ ቦርዱ ውስጥ ያሉ ሠራተኞች የውሳኔያቸው ነፃነት የሚለካው፤ እነሱ ራሳቸው በሥራቸውና በኃላፊነታቸው ላይ ባላቸው መተማመን ነው። ይህ ደግሞ በሚሰጡት ውሳኔ፤ "ይኼ ይደርስብኛል" ወይንም "እንደዚህ ብወስን ይኼንን እጠቀማለሁ" የሚል የግል ህይወታቸውን ከፊታቸው ከተደቀነው የሥራቸው ኃላፊነት ጋራ ማያያዝ እንዳይኖርባቸው ሲደረግ ነው። ይህ ደግሞ በኢሕአዴግ ግዛት የማይታለም ነው። "ሁሉም ነገር ለጦርነት!" ይል ነበር መንግሥቱ ኃይለማርያም። አሁን ደግሞ "ለሁሉም ነገር እኔ የምለው ብቻ!" ባይ በቦታው ተተክቷል። እንግዲህ ከዚህ ተነስተን፤ ምን ዓይነት ምርጫ እንደሚካሄድ እንኳን ለኢትዮጵያዊ ለባዕድም ግልፅ ነው።

# ከምርጫው በስተጀርባ

## ምርጫውና ጀርባው

ኢሕአዴግ ምርጫውን ሊኮፈስበት ይፈልገዋል። ህዝቡ ደግሞ ያለውዴታው ተገዶ ድምፁን ይሰጣል። የአምባገነኖች ባህርይ ነውና፤ ኢህአዴግ ከፍራቻው ብዛት አስቀድሞ ለማቸነፍ ሁሉን ነገር አዘጋጅቷል። እሱ ያልፈቀደው ተመራጭ አንድ ድምፅ እንኳን ማግኘቱ እንቅልፍ ስለሚነሣው፤ በምርጫው ማግሥት ትልቅ ዘመቻ ያደርጋል። የተቃዋሚው ንብረት ይዘረፋል። ሰዎች ይታሠራሉ። ብዙዎች አካላቸው ይጎድላል። ይሰደዳሉ። የተወሰኑ ሰዎች ሕይወታቸውን ያጣሉ። እኛም ከውጭ የህዝቡን ብሶት ለማሰማት የምንችለውን እናደርጋለን።

ከዚያ በፊት፤ አሁን፤ ምርጫው ከመደረጉ በፊት፤ ምን ብናደርግ ይሻላል? አሁን የምናደርገውስ ለበኋላው ፀፀታችን ማስታገሻ ሊረዳን ይችል ይሆን?

<u>እስከመቼ</u> አዎን ትላለች። በመጀመሪያ ምርጫውን የትግል ሜዳ አድርገን እንጠቀምበት። በአኳያው ከወዲሁ አቀናባሪ አሁን አቋቁመን እንዘጋጅ። ዜና ከህገር ቤት በትክክል እንዲደርሰን፤ ሟቾች በቁጥር የምንዘክራቸው ሳይሆን፤ ስማቸውን፣ አድራሻቸውን፣ ፎቶአቸውን እንድናገኝ፤ እንዘጋጅ። የማንም ድርጅት አባል ይሁኑ አይሁኑ በህዝብና በፀረ ህዝቡ ኢህአዴግ መካከል ባለው ግብግብ፤ የተሰው የህዝብ ወገንተኝነታቸው ያነሣሣን። እያንዳንዳችን በኢትዮጵያዊነታችን አሁን ማድረግ የምንችለውን ሳናደር፤ በኋላ እንዲህ መደረግ ነበረበት ብንል፤ ሌላ ሰው ሳይሆን የገዛ አዕምሯችን ይታዘበናል።

ለዚህ ቅንብር የ<u>እስከመቼ</u> የቦርድ አባላትና ከኛ ጋር የኢሜል ልውውጥ በማድረግ ሊተባበሩን ቃል የገቡት ዝግጁ ነን። ይኼ የኔም ኃላፊነት ነው ብሎ የሚጠራን ድርጅት ካለ እሰዬው እንመጣለን። በግለሰብ ደረጃም እኔ አለሁ ባይ ካለ በደስታ እንተባበራለን። አድፍጦ ጠባቂው ካየለ ደግሞ ኃላፊነቱን ወስደን የምንችለውን ከማድረግ ወደኋላ አንልም። <u>አንባቢ ሆይ!</u> ኢትዮጵያ የሁላችን ናት። ይህ ትግል የሁላችን ነው። ግንባር ቀደም ተሰልፈው የሚዋደቁትን ዝም ብለው ያያሉ!

**ከእስከመቼ ቦርድ**
ድረስ ነጋ፣
eske.meche@yahoo.com